የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 64
ADDIS ABABA 23rd May 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፵፬/፪ሺ፫

የጅማ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.....ገፅ ፭ሺ፰፻፸፬

CONTENTS

Regulation No. 240/2011

Jimma University Re-establishment Council of Ministers Regulation..... Page 5874

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፬/፪ሺ፫

ጅማ ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የጅማ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፬/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. መቋቋም

፩/ ጅማ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል።

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል።

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል።

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 240/2011

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE JIMMA UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Jimma University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 240/2011".

2. Establishment

1/ The Jimma University (hereinafter the "University") is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

ፎ. ዋና ግቢ

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ጅማ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል።

፬. የተሻረ ደንብ

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፫/፲፱፻፺፱ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. Main Campus

The University shall have its main campus at Jimma and may establish elsewhere other academic units and centres of research and community services.

4. Repealed Regulation

The Jimma University Establishment Council of Ministers Regulation No. 63/1999 is hereby repealed.

5. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of May, 2011.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሳሙኤል ግርማ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ

Samuel Girma
Legal consultant and Attorney

+251911190299

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት